## ተፈጸመ ትስብእት፡ በኢትዮጵያ ማርያም ድንግል!
## በብሥራተ ቅዱስ ገብርኤል፡ ዜናዌ ቃል!

ይድረስ፡- በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ክህነታዊ ባልደረባዬ ለኾንኸው፡ ለተወደድህና ለተከበርህ ኪዳናዊ ወንድሜ ፈቃደ-ሥላሴ።

በትናንትናው ሓሙስ፡ ታኅሣሥ ፴ ቀን፥ ፳፻፲ ዓመተ ምሕረት የጻፍህልኝ እ-ጦማርህ ደረሰኝ፤ እግዜር ይስጥልን!

በአጭር የገለጽኸው አሳብህ፡ በኹለንተናው፡ አጥጋቢና አርኪ፥ ምጡቅና ጥልቅ የኾነ መልእክትን የያዘ ነው። እንዲህ ለመኾኑ፡ ለእኛ፡ ሌላ ማስረጃና ማረጋገጫ አያስፈልገንም። አንተው እንዳልኸው፡ ጸሓፊው አንተ፡ ስሜትህን በገለጽህበት፡ በዚያው ቅዱስ ኪዳናዊ መንፈስ ኾነን ስለምንመለከተው ነው። ሊኾንም የሚገባው ይኸው ነውና።

አዎን! ከውስጥ፡ ከእየራሳችን አሥርፀን የምናስበውንና የምናሰላስለውን፥ የምናልመውንና የምንወጥነውን፥ በቃል የምንናገረውንና በእጅ የምንጽፈውን፥ የምንሥለውንና የምንቀርጸውን፥ የምናንፀውንና የምናደርገውን፥ በውጭም፡ ከሌላው የምንሰማውንና የምናየውን፥ የሚያጋጥመንንና የሚደርስብንን፡ ማናቸውንም ኹኔታ፥ ወይም ነገር ኹሉ፡ በየኅሊናችን መነጽር አጥርተን፥ በሚዛኑም መዝነን፡ የመንፈስ ቅዱሳዊው አካላችንና ባሕርያችን ፍሬ መኾኑን ከተረዳንና ካረጋገጥን፡ ልንቀበለው ይገባል።

በአንተና ለአንተ፥ ስለአንተም፡ እየኾነ በምናየው ኹሉ፡ እኔም ኾንሁ፡ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን፡ ኹላችንም፡ ከዚህ የበለጠ የሚያስደስተን፥ ተመስጋኞቹንም የሚያስመሰግነን፡ "ሌላ ኹኔታ ይኖራል!" ብለን፡ የምንጠብቀው ጸጋ፡ ከቶ የለም። በተለይ፡ ስለምንነትህና ማንነትህ፡ ራስህን፡ በፍጹም ትሕትና አዋርደህ፡ አንተነትህን ከመደብህበትና ከገለጽህበት ኹኔታ የተነሣ፡ ስለሚደርሰው ትንግርት፡ በአንተው ኪዳናዊ መንፈስ ኾነን፡ አጥርተን ስንመለከተውና አስተውለን ስንመዝነው፡ ምን እንደሚመስል እገልጽልህ ዘንድ ፍቀድልኝ!

በምድር ላይ፡ በእኛ፡ በኪዳናውያኑና በኪዳናውያቱ ልጆቻቸው ዘንድ በተከሠተችው፡ በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት የምናካኼደውን፡ የደስታችንን ዓይነትና መጠን፡ ለፍጹምነት አብቅቶ፡ በዚሁ ጊዜ፡ በሰማያት፡ በዘለዓማውያኑ ወላጆቻችን፡ በእግዚአብሔር አብና በእግዚአብሔር እም፥ በዘለዓለማዊው ወንድማችን፡ በእግዚአብሔር ወልድና በዘለዓለማዊው ባልደረባችን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፥ እንዲሁም፡ በቅዱሳን ባልንጀሮቻችን ጻድቃንና ተባባሪዎቻችን መላእክት ዘንድ ከሚደረገው ታላቅ ሓሤት ጋር፡ ተመሳሳይ እንደሚያደርገው የተረጋገጠበት፡ መለኮታዊው እውነታ ነው። ያም እውነታ፡ በሉቃስ ብሥራት፡ በምዕራፍ ፲፳ በተነገረው የምሥራች ቃል፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ከታወጀ፡ እነሆ፡ ኹለት ሽህ ሰባተኛ ዓመቱን ይዞ፡ በኀላ ድምፅ መሰማቱን ቀጥሏል።

በሰማዩ አባታችን ሰላም እና በሰማይዋ እናታችን ፍቅር፡ ከየኪናዳዊው ቤተሰባችን ጋር፡ ኹላችንንም፡ በያለንበት፡ በደኅና የሚጠብቀን፥ በበጎውም የሚመራን መንፈስ ቅዱስ፡ የማያቋርጠው ምስጋናችን ይድረሰው!

ጥር ፪ ቀን፥ ፳፻፲ ዓመተ ምሕረት።

ኪዳናዊ ወንድምህና ክህነታዊ ባልደረባህ፡-
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ።